ያላቸው ድርጅቶች ለመፍጠር ነበር ። ቦዘኔዎች በነዚያ ድርጅቶች አማካይነት በማህበራዊ ኑሮና በኤኮኖሚ እርስ በርስ ለመረዳዳት እንዳንዴም የሚጨቁኗቸውን ቢሮክራቶችና የመሬት ከበርቴዎች ለመዋጋት ይጠቀሙባቸው ነበር ። እርግጥ ነው ፤ እንደነዚህ አይነቶቹ ወደ ኋላ የቀሩ ድርጅቶች ለገበሬዎቹና ለእደ ጥበብ ሙያተኞቹ መውጫ መንገድ አልሰጧቸውም ። በተጨማሪም ፤ በመሬት ከበርቴዎቹና በቀበሌ ገገርዎቹ ቁጥጥር ስር በቀላሉ በመዋል ሊጠቀሙባቸው ይችሉ ነበር ። በዚህና እንደዚሁም ጭፍን ሆነ አጥፊነታቸው ምክንያት ለጥቂቶቹ ወደ አድሃሪ ሃይሎች ተለውጠው ነበር ። ቺያንግ ካይሼክ በ1928ቱ ፀረ አብዮት መፈንቅለ መንግስቱ የሰራተኛውን ህዝብ አንድነት እንዲበጠብጡና አብዮቱን እንዲያወድሙ ተጠቅሞባቸዋል ። ዘመናዊ የኢንዱስትሪ ወዛደር ተነስቶ እየተጠናከረ ሲሄድ ገበሬዎች በሰራተኛው መደብ መሪነት ቀስ በቀስ ፍፁም በአዲስ አይነት ድርጅቶች ስለተቋቋሙ እነኛ ጥንታዊና ወደ ኋላ የቀሩ ማህበሮች ህልውናቸውን አጥተዋል ።



# በገጠር ያሉት መደቦች እንዴት እንደሚታዩ

ጥቅምት 1933

## 1/ የመሬት ከበርቴው

የመሬት ከበርቴ መሬት ያለው ፤ ራሱ በስራ ላይ የማይሳተፍ ወይም እጅግ አነስተኛ በሆነ ደረጃ የሚሳተፍና ገበሬዎቹን በመበዝበዝ የሚኖር ሰው ነው ። የመሬት ኪራይን መሰብሰብ ዋነኛው የብዝበዛ መሣሪያው ፤ በተጨማሪም ገንዘብ ሊያበድር ጉልበት ሊቀጥር ወይም ደግሞ በኢንዱስትሪ ወይም በንግድ ተግባር ሊሰማራ ይችላል ። ይሁንና ከገበሬዎቹ የመሬት ኪራይን ማጋበስ ዋነኛው የመበዝበዣ መሳሪያው ነው ። የጋርዮሽ መሬትን ማስተዳደርና የትምህርት ቤት ቦታዎችን ኪራይ መሰብሰብ በመሬት ኪራይ የብዝበዛ ዘርፍ ውስጥ ይጠቃለላል ።

በስራ ላይ የማይሰማራና ግን ሌሎችን በማጨበርበር ወይም በመዝረፍ ወይም ከስጋ ዘመዶቹ ወይም ከጓደኞቹ እርዳታን በማግኘት የሚኖርና ከመደበኛው የመሀከለኛው ገበሬ በኑሮ የሚሻል የከሰረ የመሬት ከበርቴ በመሬት ከበርቴነት ይመደባል ። የጦር አበጋዞች ባለ ሥልጣኖች ያካባቢ ጨቋኞችና ሐኬተኞች የበታች መኳንንት የመሬት ከበርቴው መደብ ወኪሎችና እጅግ ጨቋኝ የሆኑ አባሎች ናቸው ። አነስተኛ የአካባቢ ጨቋኞችና ሀኬተኛ መኳንንት ብዙውን ጊዜም ከሀብታም ገበሬዎች መሀከል ይገኛሉ ።

የመሬት ኪራይ በመሰብሰብና ንብረቱን በማስተዳደር የመሬት ከበርቴውን የሚረዱ ለዋና ገቢ ምንጫቸው በመሬት ከበርቴው የገበሬዎች ብዝበዛ ላይ የሚመኩና በኑሮአቸውም ከመደበኛው መሀከለኛ ገበሬ የተሻለ ሁሉ ከመሬት ከበርቴዎች ፈርጅ ውስጥ ይመደባሉ ። አራጣ አበዳሪዎች የአራጣ ማበደር ብዝበዛን እንደ ዋና ገቢ ምንጫቸው ያደረጉ ፣ ከመደበኛው መሀከለኛ ገበሬ የተሻለ የሚኖሩ ሰዎች ናቸው ስለዚህም ከመሬት ከበርቴው ፈርጅ ውስጥ ይመደባሉ ።

## 2/ የሀብታም ገበሬ መደብ

ሀብታም ገበሬ በመሠረቱ መሬት አለው ፤ ሆኖም ጥቂት ሀብታም ገበሬዎች ከሚያርሱት መሬት ከፊሉ ብቻ የራሳቸው ሲሆን የተቀረውን ይከራያሉ ። ሌሎች የራሳቸው የሆነ ምንም መሬት የላቸውም ስለዚህም የሚያርሱትን መሬት በሙሉ ይከራያሉ ። አብዛኛውን ጊዜ ሀብታሙ ገበሬ ከመሀከለኛው ገበሬ በጣም የተሻሉ የማምረቻ መሳሪያዎችና ጥሬ ገንዘብ ያለውና በሥራውም የሚሳተፍ ነው ። ሆኖም አብዛኛውን ጊዜ ከገቢው በከፊል እንዲያውም አብዛኛው ብዝበዛ ላይ ያተኮረ ነው ። ዋናው የብዝበዛ መሳሪያው የጉልበት ሰራተኞችን (የረዥም ጊዜ ሰራተኞችን) መቅጠር ነው በተጨማሪም ፣ ከመሬቱ በከፊል በማኮናተር በመሬት ኪራይ ብዝበዛ ሊሳተፍ ይችላል ። ሰፋ ያለ መሬት ያለው ከፊሉን ሰራተኞች ሳይቀጥር ራሱ የሚያርስ ሆኖም ሌሎችን ገበሬዎች በመሬት ኪራይ ወይም በወለድ ብድር ወይም በሌላ መንገዶች የሚበዘብዝ ሰው እንደ ሀብታም ገበሬ ይቆጠራል ሀብታም ገበሬዎች ብዝ



በዛን መደበኛ ተግባራቸው በማድረግ አብዛኛዎቹ ከገቢያቸው ከፍተኛው ክፍል ከዚሁ ምንጭ ያገኛሉ ።

## 3/ መሀከለኛ ገበሬ

ብዙዎቹ መሀከለኛ ገበሬዎች የመሬት ባለቤት ናቸው ጥቂቶቹ ከያዙት መሬት ከፊሉ ብቻ የራሳቸው ሲሆን የተቀረው የኪራይ ነው የተቀሩት የራሳቸው የሆነ ምንም መሬት የላቸውም ስለዚህም የያዙትን መሬት በሙሉ ይከራያሉ ። ሁሉም መጠነኛ የእርሻ መሳሪያ አላቸው ። መሀከለኛ ገበሬ ገቢውን በሙሉ ወይም አብዛኛውን የሚያገኘው ከራሱ የስራ ፍሬ ነው ። በመሰረቱ ሌሎችን አይበዘብዝም ፤ እንዲያውም ብዙውን ጊዜ መጠነኛ የመሬት ኪራይና የብድር ወለድ መክፈል ስላለበት ራሱ በሌሎች ይበዘበዛል ። ቢሆንም በአጠቃላይ ሲታይ ጉልበቱን አይሸጥም ። ጥቂት መሀከለኛ ገበሬዎች (ሀብታም የሆኑ መሀከለኛ ገበሬዎች) መጠነኛ ብዝበዛ ያካሂዳሉ ፤ ሆኖም ይህ መደበኛ ወይም ዋነኛ የገቢ ምንጫቸው አይደለም ።

## 4/ ድሀው ገበሬ

ከድሀ ገበሬዎች መሀከል ጥቂቶቹ ከሚያርሱት መሬት ውስጥ ከፊሉ የራሳቸው ሆኖ ጥቂት ያልተሟሉ የእርሻ መሳሪያዎችም አሏቸው ፤ ሌሎች ጥቂት ያልተሟሉ የእርሻ መሳሪያዎች እንጂ ምንም መሬት የላቸውም ። በመሰረቱ ድሀ ገበሬዎች የሚያርሱትን መሬት መከራየት አለባቸው ፤ ስለዚህም የመሬት ኪራይና የብድር ወለድ ስለሚከፍሉ በመጠኑም ራሳቸውን ለሌሎች ስለሚያስቀጥሩ ለብዝበዛ

የተጋለጡ ናቸው ። በአጠቃላይ ድህው ገበሬ ከጉልበቱ ከፈሉን መሸጥ ሲኖርበት ፣ መሀከለኛው ገበሬ ግን ጉል በቱን መሸጥ አያስፈልገውም ። መሀከለኛውንና ድሀውን ገበሬ የመለያ ዋናው ሚዛን ይህ ነው ።

## 5/ ወዛደሩ

ወዛደሩ (የእርሻ ወዛደሩን በመጨመር) ምንም እን ኳን ጥቂቶቹ ትንሽ መሬትና በጣም ጥቂት የእርሻ መሳ ሪያዎች ቢኖራቸውም በመሰረቱ መሬትም ሆነ የእርሻ መሳሪያዎች የለውም ። ወዛደሮች ኑሮአቸውን ሙሉ በሙሉ ወይም በይበልጥ የሚገፉት ጉልበታቸውን በመሸጥ ነው ።

## ማስታወሻ

በቻይና የገጠር አካባቢዎች የተለያዩ የሕዝብ መሬት ይዞታዎች ነበሩ……በከተማ ወይም በቀበሌ አስተዳደር በአንድ ጎሳ ጥንታዊ ገዳም በቡዳህዊ ወይም በታኦዊስት ገዳም ፣ በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ወይም በመስጊድ የተ ያዘ መሬት ወይም ገቢው ለሕዝቡ በጎ አድራጎት ተግባ ሮች እንደ ረሀብ እርዳታ ወይም ድልድዮችንና መንገዶችን ለማሰራትና ለመጠገን ለመሳሰሉት ወይም ለትምህርታዊ አላማዎች የሚውል መሬት በተግባር ከዚህ መሬት አብ ዛኛው በመሬት ከበርቴዎችና በሀብታም ገበሬዎች ቁጥ ጥር ስር ነበር ስለዚህም ጥቂት ገበሬዎች ነበሩ በአስተ ዳደሩ አነስተኛ ድምፅ የነበራቸው ።



